# "የነገው ሰው" የጥሪ ደወል ለያ . . . ሰው

*ሰኔ 25, 2000 ዓ.ም. (July 02, 2008) የተፃፈ፤ እውነታው ዛሬም አለ።*
*ጊዜን ጨምሮ መጠነኛ መስተካከል ታክሎበት*
*ነሲቡ ስብሐት*

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከመቼውም በከፋ ሁኔታ ላይ በመገኘቷ ልጆቿን ትጠራለች። ህልውናዋ አስጊ ሁኔታ ላይ በመሆኑ ዜጎቿ ያድኗት ዘንድ እየተማጸነች ነው። ሀገራችን አሁንም ለክብሯና ለነፃነቷ የሚሰዉላትን እየፈለገች ነው። ልጆቿ ነንና የዜግነት ግዴታችንን እንወጣ ዘንድ ትጣራለች። ከሁሉም ይበልጥ ደግሞ ታሪክ ተረካቢውና ሀገር ተረካቢውን ትውልድ፣ ወጣቱን ትውልድ ታያለች። የነገው ሰው ናችሁና አትጡኝ ትላለች።

ዛሬ ወጣቶች ተሰባስበውና ተደራጅተው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው አይታዩም። በየግል የሚወሰደውን እንቅስቃሴ እስከ መስዋትነት መክፈል እያሳዩን ነው። ግና የተጠናከረና የተባበረ ቤት የላቸውም። ለምን?

ለብዙ ዓመታት ለሀገርና ሕዝብ ነፃነት የተጋደሉና እየታገሉ ላሉ ለጥንካሬአቸው ምስጋና ይግባቸውና  ተዋግተዋል። ታግለዋል። ግና ለድል ለመብቃት አይደለም፣ ለመብቃት የሚያስችላቸውን ኃይል መገንባት አልቻሉም። የትግሉን ዋልታና ምሰሶ ረስተውታልና። ዘንግተውታል።

ትግሉ የነፃነት ነው። ለዚህ የነፃነት ትግል ሊታቀፍ የሚገባው መታቀፍ ይኖርበታል። የትግሉ ሞተር ቁልፍ ተዘንግቶ ተራራው ቁልቁለት አይሆንም። ለዚህም ነው የሚያንሸራትተው። ተራራውን ለመውጣት ምርኩዙ ወጣቶች ናቸውና።

ውድ ወገኖቼ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ በልጆቿ ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ምኞታችን ነው። ይህን ዛሬ አላየነውም። ዛሬ ሀገራችን ተደፍራለች፣ ክብሯን አታለች። ነገ በማን ዘመን ነው? በየትኛው ትውልድ ነው? ሀገርና ትውልድ ይጠይቁናል። ሀገራችን፣ ሕዝባችን አንድ ቀን የነፃነት አየር ይተነፍሳሉ። ድል ይቀዳጃሉ። ግና ኢትዮጵያችን ለሁሉም እፎይ ብላ የልጆቿ የምትሆንበትን መሠረት ጥለናል ወይ? አስበንበታል ወይ? ወደድንም ጠላን ይህች ሀገር የሚረከባት አዲስ ትውልድ ነው። ያረጀው ይሄዳል፤ አዲስ ይመጣልና። ምን እያስተማርናቸው ነው? ወጣቶችን። ልጆቻችንን ሀገራቸውን እንዲያውቁ፣ እራሳቸውን እንዲያዩ ምክራችን ምንድን ነው? "እኔ የገባሁበት ፖለቲካ ይበቃል፣ አርፈህ ኑሮህን ኑር፣ ትምህርትህን ተማር" ይህንን ነው ልናወርስ የተዘጋጀነው። ምን ነገርናቸውና፣ ምን አስተማርናቸውና ይከተሉን። መባላትን፣ አለመስማማትን፣ ለሀገር ሳይሆን ለግል ማሰብን፣ ስለ ሕዝብ የበላይነት ተረስቶ የድርጅት ቀደምትነትን፣ ስለ ሰፊዋ ሀገር ሳይሆን ስለ ጠባቧ።

ታሪክን ዘወር ብለን ለመቃኘት ፍላጎቱ ካለን የዛሬ አባወራዎች የወጣትነት ዕድሜአችሁን ስታሰሉ ያንን ጀግንነት ከየት አመጣችሁት? ለሀገር መሰዋትን፣ ለወገን እኔ ልቅደምን፣ እኔ ልሙትን በተግባር ያስረገጠ ትውልድ ብቅ ብሎ ድርግም ያለበት ዘመን እንዴት ተፈጠረ? ከምን መጣ? የፖለቲካ ድርጅት የፈጠረው ተዓምር እንዳይመስላችሁ። በተግባር የታየው ጀግንነት ግን አባቶቻችን፣ እናቶቻችን ያወረሱት ነው። ያስተማሩት። ሀገር መጠበቅን፣ ለሀገር መሰዋትን፣ ለቆሙለት ዓላማ በጽናት መቆምን ተርከዋልና። በተግባር አሳይተዋልና። እነሱ ያወረሱት ጀግንነት ነው የተገበረው። የነሱን ኑዛዜ ነው ተግባራዊ የተደረገው። ቃል ኪዳናቸው ነው የተፈጸመው።

በሀገር ጉዳይ ላይ የፀና አቋም እንዲኖር ቅድሚያው ሀገርን ማፍቀር ነው። ይህ የሀገር ማፍቀር ስሜት የሚፈጠረው ደግሞ ከትውልድ ትውልድ በተወረሰ ታሪክ፣ ወግና ባህል ውስጥ በማለፍ ነው። ቤተሰባዊ አስተዳደጋችን፣ ሃይማኖት፣ የትምህርት ተቋማት፣ ኪነ ጥበብ ዘርፎች፣ ባህላችን የእነኚህ ውጤት ሁሉ በሀገር ፍቅር ስሜት ተኮትኩተን እንድናድግ ያደርገናል። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ታሪክ ወግና ባህል ለወጣቶች ያወርሱታል። ለሀገር መሞትና ለሀገር ቤዛ መሆንን የሞራል መሠረት ይጥሉለታል።

- በላይ ዘለቀ ተሰቅሎ "እምቢኝ ለሀገሬን" አስተምሮናል።
- ዓፄ ተዎድሮስ በሽጉጣቸው ለጠላት እጅ አለመስጠትን፣ አለመንበርከክን የጅግና ሞት ሞተው አስተምረውናል።
- አፄ ዮሐንስ ለሀገራችን ሉዓላዊነትና ለግዛታችን አንድነት አንገታቸውን በመቀላት ተምረን እንድናስተምር አሳይተውናል።
- አፄ ምኒሊክ በአድዋ ጠላትን ድል ማድረግን አስተምረውናል። አውርሰውናል።
- እቴጌ ጣይቱ ብጡል በሴትነታቸው ብልጠትን ከጀግንነት ሜዳው ጽፈውልናል።

ይህንን ውርስ ነው ያ ትውልድ፣ ያ ወጣት የመሰከረው። ዛሬ በዚያ ዘመን እየተባለ የዕድሜ ማስሊያ ብቻ እንዲሆን መተው የለበትም። የዚያ ትውልድ ታሪክ በተለይ ደግሞ የሀገር ወዳዱ ወጣት ታሪክ ደብዝዞ እንዲጠፋ፣ ጠቁሮና ከፍቶ እንዲጠላ፣ ረክሶ እንዲናቅ የሚደረገው ጥረት ሊያሳስብ ይገባል። ታሪክ በአግባቡ ለትውልድ ይተላለፍ ዘንድ ጊዜውን መጠቀም ግድ ይላል። ጊዜ በበረረ ቁጥር ሞትን ድል እንደማያደርግ ልንገነዘብ ይገባል።

ተሸክመን የምንጓዘውን መዘንጋት የለባችሁም። እሱ እኮ ነግሮ አይመጣም። ልወስድህ ነውና ተዘጋጅ አይለንም። ዛሬ በትግሉ አውድማ ያሉቱ አብዛኛው ከጋሼ ወድ አባባ፣ ከእትዬ ወደ እማማ የዕድገት ደረጃ ላይ ናቸው። በመሆኑም ሀገር የማዳን ጉዞው፣ የነገዋ ኢትዮጵያ የዜጎቿ ትሆን ዘንድ ተተኪ፣ ተረካቢ ግድ ይላል። ወደ ማይቀረው የዘላለም ቤት ደጃፍ ተደርሿል። ሀገራችን ግን ሁሌም ትኖራለች። እናሳ? እናማ ሀገር እንድትኖር፣ የነገ ሕይወቷን የምትመኙ ከሆነ ንብረታችሁን እውርሱ። ወጣቶችን እናስተምር። ወጣቶችን እንከባከባቸው። እንያቸው። እናናግራቸው። እናዳምጣቸው። የማይገፋውን ዳገት የሚገፉት እነሱ ናቸውና። አዎ! ለራስ ስልጣን አስፈላጊ አይደሉም። አዎ! ለግል ስልጣን፣ ለግል ክብር ሚናቸው ውሱን ነው። ለሀገርና ለሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ከሆነ ግን የትግሉ ሜዳ ላይ ወጣቶች ማጀብ ሳይሆን መታጀብ ይገባቸዋል።

በዘመነ ደርግ የ7እና 10 ዓመት ሕፃናት ሬሳ እያዩ ነው ያደጉት። በወንድምና እህታቸው ላይ "ቀይ ሽብር ይፋፋም" እያሉ ነው ያደጉት። በጨቅላ አዕምሯቸው በየጊዜው ስለ ግድያ ሲዘመርላቸው ነው ያደጉት። ዛሬ እኚህ ወጣቶች በ40 ዕድሜ ክልል ሚገኙቱ በፍርሃት ተገንነት ጨለማ ይዟቸዋል። በወያኔ የ7ና 10 ዓመት ሕፃናት ዛሬ በ30ው ዕድሜ ክልል ይገኛሉ። ለ27 ዓመታት ስለ ዘረኝነት፣ ስለ ጉሳ ፖለቲካ፣ ስለ ጠባብነት እየተሰበኩ፤ ኢትዮጵያዊነታቸውን እየዘነጉ፣ እየረሱ እንዲያድጉ ነው የተደረጉት። እናም ፍርሃትና ዘረኝነት ተባብረው ልጆቻችንን ይዘዋቸዋል። እኛም ደግሞ ማራቁን ከመረጥን፣ ማስተማሩን ከነፈግናቸው፣ አናስጠጋ ካልናቸው፤ እየደነገጡ፣ ግራ እየገባቸው፣ የሚያዩት አልታይ እያላቸው፣ የሚያዳምጡት አልሰማ እያላቸው፣ የሚፃፈው አልነበብ እያላቸው ነው የሚጓዙት። ይህ ደግሞ ከተስፋ መቁረጥ ጋር መጤ ባህሎችን ቢያፈቅሩ፣ ሀገራቸውን ከመምሰል ይልቅ ሌላውን ቢመስሉ፣ በባህላቸው ቢያፍሩ፣ በቋንቋቸው ባይግባቡ ልንፈርድባቸው አግባብ አይደለም። እንዴት ደርሰን እናድናቸው? ተብትቦ ከያዛቸው መርዝ እንዴት እንፈውሳቸው? የበሽታው መድኃኒቱ የቱ ነው? ይህንን መመለስ ስንችልና ስንደርስላቸው ያን ጊዜ ሀገር ዳነች። ያን ጊዜ ሀገር ተኪ ዜጋ አገኘች። ያን ገዜ ሀገር ሉዓላዊነቷና አንድነቷ ተጠብቆ እንደሚኖር እናስረግጣለን። ተስፋችንም ልምላሜ ያገኛል።

የዛፉ ቅርንጫፍ ይበዛል። ይህ ካልሆነ ለደካማ ጐናቸው ተባባሪ ከሆንን፣ እያየን እንዳላየን ካለፍነው ነገ ለሚከሰተው ውጤት የእኛም እጅ እንዳለበት መዘንጋት አይኖርብንም። ልጄ ሆይ! ብለን ድምጽ ማሰማቱ ተስኖናል። አሁንም እኛን እንዲያዳምጥ እንፈልጋለን። አሁንም እኛን እንዲያይ እንፈልጋለን። መንገዱ ይህ አይደለም። እስቲ እዳምጧቸው፣ እስቲ እበረታቷቸው፣ እስቲ ተረከቡን በሏቸው፣ እስቲ መካሪ ሁኗቸው። የነገ ሀገር ተረካቢ ናቸውና። የነገዋ ኢትዮጵያ የነሱ ናትና። አሁን የአለውን ሁኔታ ጥለንላቸው ከሄድን ግን ብዙ ጥፋት ይኖራል። እራሳችንን መርምረን አንድነትን ልናስተምራቸው ይገባል። እራሳችንን ጠይቀን ኢትዮጵያዊነትን ልንተርክላቸው ግድ ይለናል። በኩራትና በክብር ዓርማችንን ልንሰጣቸው ይገባል። ውስጣችንን አነጋግረን ያለንን ሀብትና ንብረት የትግል ተመክሮ ምስጢረ ተዓምር አይደለምና ሳንቆጥብ፣ ሳንሰስት፣ ሳናዛንፍ ልናስረክባቸው ይገባናል። አንፍራቸው ወጣቶች ናቸውና። አናርቃቸው እያዩን ነውና። አንሸሻቸው እየተከተሉን ነውና። ወጣቶች ወደኛ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው። ነገ የነሱ ናትና። የልጅ ነገር አንበላቸው የልጅ አዋቂዎች ናቸውና። የኛው ጣጣ ነው በጨለማ ያሰራቸውና በነሱ አንፍረድ።

ዛሬ ሀገራችንና ሕዝባችን ከባድ ፈተና ከፊታቸው ተደቅኗል። ዛሬ የለውጥ ሐዋርያ ሆነው አቶ ለማ መገርሳና ዶር ዐቢይ አሕመድ ብቅ ቢሉም አገዛዙ ላይ ወያኔ/ህወሓት እና አንዳንድ የዘር ድርጅቶች አሁንም ሚናቸው አልከሰመምና ኢትዮጵያን ሊበታትኗት የዕቅዳቸው የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሰዋል። የወያኔ/ህወሓት የመጨረሻ ደረጃ ኢትዮጵያን መበታተን ነውና። ህወሓት/ወያኔ በ27 ዓመት አገዛዙ በዝርፊያው እጅግ ጠግቧል። በግድያው በአፈናው አራራውን ተወቷል። በዘረኛ ጅራፉ ሁሉንም ገርፏል። በሁሉም አቅጣጫ የሀገራችን እልውና አጠያያቂ ደረጃ ላይ ነው። በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በምዕራብ ኢትዮጵያ በየቀኑ የሚሰማው ዜና ማህበረሰብ ገጾችን አጣቦ ይገኛል። ወያኔ በቁማችን ለባዕዳንና ለተወሰኑ ቱጃሮች እንደሸጠን ሁሉ ዛሬ ሀገር የሕዝብ ሳትሆን የወያኔና የተወሰኑ ቱጃሮች በተጨማሪም የኢትዮጵያን አንድነት በማይፈልጉ ባዕዳንና ዘረኞች ተባባሪነት ልትበጣጠስ ነው። የመበታተን ቦምቡ ተጠምዷል። ልናከስመው ግድ ይለናል። ይህን የምንተገብረው ትኩሱን ኃይል አነሳስተን ነው። ሀገሩን ይወዳልና። ለሀገሩ መስዋትነት ይከፍላልና። በተቀናጀ መልክ ይሆን ዘንድ ወጣቱ ትውልድ የሚያስተባብረው ነው ያጣው። ትብብርነቱን፣ መሰባሰቡን፣ መደራጀቱን፣ ማስተማሩን ዛሬ ከአደረግነው ለነገ የሀገራችን ራዕይ የተዘጋጅ ኃይል አለና እፎይ ብትሉ አይፈረድባችሁም። ተክታችኋልና። አምርታችኋልና። ዛሬ የተተከለው ችግኝ ነገ ያፈራልና። ዛሬ ወጣቱን የሀገር ውኃ ማጠጣት ይጠበቅባችኋል። መኮትኮት ያስፈልገናል። ለኛ ሳይሆን ለሀገሩ እንዲያስብ መምከር ይጠበቅባችኋል። ቅድሚያችን ሀገር ናትና።

ጥረቱ ሀገር በድል አድራጊነት እንድትወጣ፣ ሁሉም ለሀገርና ለሕዝብ ተሚጋች ዘብ ቋሚ፣ ጠበቃ ኃይል እንዳይሳሳ፣ ጠንክሮ እንዲገኝ፣ ታሪክ እንዳይበረዝ፣ እንዳይበላሽ፣ ያልነበረው እንደነበረ እንዳይተረክ፣ ውሸት ሃቅን እንዳያሸንፍ፣ ወደ ልጆቻችን እንጓዝ። ይህን ስታደርጉ ኃላፊነታችሁን ተወታችኋል። አደራ አስረክባችኋል። የታሪክ ዕዳችሁን ከፍላችኋል። ይዘነው ከተቀበርን፣ እጅና እግራችንን አጣጥፈን ከተቀመጥን ማየቱ ካቃተን፣ መናገሩና ማድመጡ ከተሳነን ነገ ትውልድና ታሪክ ቢወቅሱን ልንቀበል ግድ ይለናል።

ዛሬ በፖለቲካው መድረክ ያሉ ተቃዋሚ/ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ልዩነታቸውን እያቻቻሉ የጋራ መድረክ ለመፍጠር ብዙ ጥረዋል። ግና ተሳክቶለት የወጣ የለም። ዛሬም የኀብረት ትግል በጥያቄ ላይ ነውና። ዛሬም የጋራ መድረክ በጥያቄ ላይ ነውና። ለምንድነው የምንመሠርተው የጋራ መድረክ ውጤት ሊያስመዘግብ ያልቻለው? ምክንያቱ ምንድን ነው? መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች በተለይ አንጋፋዎቹ በርግጥ በጥንት ዘመን በነበረባቸው ልዩነት አሁን በጋራ መድረኩን ሲጋሩ መተማመንን ፈጥረዋል? ወይስ በጥርጣሬ

እየተጓዙ ነው? ድርጅቶች ምን እያደረጉ ነው? እየተንቀሳቀሱ ነው? እውን ስብስቡ ሕዝብን መሠረት ያደረገ ነው? ይህን ስናይ ቅራኔን ያላዘለ፣ ቂምን ያልቋጠረ አዲስ ትውልድ፣ አዲስ ሀገር ተረካቢ ኃይል እንኳ ለማፍራት ከተጣረ አንደኛውን የታሪክ አደራ ተወታችኋል። መፈራራት፣ አለመተማመን፣ ጥርጣሬ አጅበውት የሚጓዝ የጋራ መድረክ ቢመሠረትም ነገ ዳግም መጮሁ አይቀርም። የኅብረት ያለህ እየተባለ። መሠረቱ የተገነባው በወጣቱና በኅብረተሰቡ አይደለምና። እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት የሀገራችንን ታሪክና የፖለቲካ ሂደት ሃቁን ሊያስጨብጡ፣ ሊሰነዝሩ ካልቻሉ ከተለያየ አቅታጫ የተለያየ ታሪክና ትረካ እየሰማ ያለው ትውልድ ላይ ግራ መጋባትንና መዘበራረቅን ነው ተቀበል የሚባለው። ይህ ደግሞ ውሉን ያጣ መነሻና መድረሻውን ያላወቀ የጨኸት ፖለቲካ ውስጥ ይዘፍቃል።

ለመሠረታዊና ለዘላቂ ጉዳዮች፣ ለሀገርና ለወገን ጥቅም ቅድሚያና ትኩረት ተሰጥቶ ድል ለመጎናጸፍ መንገዱ ክፍት ነው። የሁላችንም ዕውቀትና ተመክሮ መሠረት አድርገን መክረን ዘክረን የምናወጣው የትግል መርሃ ግብር፣ የምንቀይሰው ሥልት፣ እንዲሁም የሁላችንም ኃይል ጥረት አስተባብረን የምናጠነክረው የጋራ መድረክ ለድል እንደሚያበቃን አያጠያይቅም። ዕድሜ፣ ጾታ፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የፖለቲካ ድርጅት ሳይለይ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የምትበጀዋን ኢትዮጵያን ከመመሥረትና ከመገንባት የሚያግደን ኃይል ከቶ አይኖርም። የሀገራችንና የወገናችን ችግር ለመፍታት እነሆ እኛም የትውልድ ግዴታችንን ለመወጣት ራሳችንን እንድናዘጋጅና የነገውን ሰው ትኩረት እንድንሰጠው ጊዜው ግድ ይላል።

ለውጥ አምጪ ወጣቶች ከዕምቅ ኃይላቸው ጋር ተደብቀዋል። ከአዲስ ፈጠራቸው ጋር ተሸፍነዋል። ጥሩ ነገራቸውን ይዘው ብቅ እንዲሉ መበረታታት ያስፈልጋቸዋል። ህዝብን ለማነሳሳት ተደማጮች ናቸው። ከሕዝብ ጋር ያላቸው ትስስር የጠነከረ ነውና እንዲጠቀሙበት፣ እንዲያወጡት አቅጣጫ መስጠት ይኖርብናል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ አስፈላጊነቱን ማመን ያስፈልጋል። መቀበል።

ዛሬ ወጣቶቻችን ሀገርን እንዲዘነጉ ተደርገዋል። በትምህርት ተቋማት፣ በሃይማኖቱ፣ በባህሉ፣ ትውልድ ሀገሩን እንዲረሳና በቀጣይነት የግል ፍላጎቱ ላይ እንዲያተኩር፣ የሀገሩ ራዕይ እንዲጠፋው ስኬታማ ባይሆንም ተቀጥቅጠዋል፣ ተሰብከዋል። ለዚህ ደግሞ ባዕዳን ኃይሎች በከፍተኛ እየገፉበት ነው። በሀገራችን ለአላቸው ጥቅም፣ በኢሕአዴግ አገዛዝ ለመሠረቱት የተለያዩ ተቋም ቀጣይነትን ይፈልጋሉ። መንግሥት ቢቀያየርም ፍላጎታቸው፣ ጥቅማቸው ዝንፍ እንዳይል ይፈልጋሉ። ስለ ዐባይ መብታችንን ይገድባሉ። ተፈጥሮ ሀብታችን ካልገቡበት፣ በነሱ በጎ ፈቃድና መሪነት ካልሆነ፣ ለነሱ በሚያመቻቸው ዕይታ ካልሆነ በመብታችን፣ በዕልውናችን የሚያደርጉትን መፈታተን ነገም ከነገ ወዲያም በተወሳሰበ መልኩ ሊቀጥሉ ይፈልጋሉ። ብሔራዊ ስሜታችንንና አንድነታችን ከተጠናከረ አሁንም ኢትዮጵያን አውራ ልናደርጋት እንደምንችል፣ ብቃቱ እንዳለን ቀድመውን ተረድተዋልና ያሰናክሉናል። ለዚህ ሁሉ ዕቅዳቸው የዘመቱት ታዳጊው ወጣት ላይ ነው። ስለ ነገ ዘረፉቸው የዛሬውን ትውልድ ማሰናከል ትልማቸው ነውና። ዘምተውበታል። በሃይማኖት፣ በዕርዳታ፣ በተለያዩ መንግሥታዊ በሆኑና ባልሆኑ ተቋማት በልማት ስም አዕምሮውን፣ አስተሳሰቡን እየሰለቡት ነው። የነገዋ ኢትዮጵያ እንዳትታየውና በሀገሩ እንዲያማርር እያደረጉት በምትኩ ባዕድ አፍቃሪ፣ ስደት ናፋቂ እንዲሆን እየተጫወቱበት እናያለን። ይህ ሁሉ ዘመቻ በዚህ አረመኔ አገዛዝ ያገኙትን ጥቅም ብቻ ሳይሆን ወደፊትም እንዳሻቸው እንዲያዙን፣ እንዲገዙን፣ መመሪያ እንዲሰጡን ይፈልጋሉና ትውልዳችን ላይ ሲዘምቱ እያየን አለመንቀሳቀስ ከተጠያቂነት አልፎ አሳፋሪ ነው። የመከላከል ብቃቱን በአግባቡ አልተወጣነውምና። የፖለቲካው ሰው፣ ምሁሩ፣ ሀገር ወዳዱ፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ሁላችንም የዕድሜ ባለፀጋዮች ስለ ነገዋ ኢትዮጵያ ካሰብን ስለ ነገው ሰው እናስብ።

"ይኖር ይሆን ወይ ባንዲራ፤ ሰውን የመሰለ አሻራ" እንዳለው ገጣሚ ደበበ ሰይፉ ወፎቹ እንዲዘምሩ፣ አራዊት እንዲቦርቁ፣ ወንዞች እንዲፈሱ፣ ዕፅዋት እንዲያብቡ ከተፈለገ የነገው ሰው ላይ እናተኩር።

***ጋሼ/እትዬ…ወገኖቼ***

*". . . እኔስ አዘንኩ ለዚህ አምባ፤ እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን*
*ለሚፎክት ለሚያቃስት፤ በመፃጉእን ደረመን*
*ለሚሰቃይ ለሚታመም፤ በአእላፍ ደዌ - ሰቀቀን፤*
*እኔስ አዘንኩ ለዚህ አምባ፤ እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን።*
*ሕፃናት መንቆር፤ ማጉርጥ ባወጡበት*
*አጥንት በተገተገበት*
*በድን - በላ በሆኑበት፤ እርመ - በላ በተባሉበት፤*
*እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን።*
*እናቶች ስብዕናቸውን በጠረጠሩበት*
*እንደትኋን እንደቅማል ዕጭ በፈለፈሉበት*
*የዕንግዴ ልጅ፤ እንደ ሕፃን በታቀፉበት*
*የራሄልን ዕንባ በዋጡበት*
*እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን።*
*አባቶች በነጭ ጠጉራቸው ባፈሩበት*
*አድባራቸውን በረገሙበት*
*ሕልማቸውን በተሳቀቁበት፤*
*ያበሻ ማቅ - ቱቢት በተፈተለበት*
*ነጭ ማተብ በተገመደበት*
*እኔስ አዘንኩ ለዚህ አምባ፤ እኔስ አዘንኩ ለዚህ ዘመን።*
*የታሪክ ደረባ ሲከፈት፤ ሲከፈት የታሪክ መዝገብ ብራና*
*መቼም ሳያኖረው አይቀርና፤ ሳይከትበው አይዘነጋውና*
*ምንድን ብሎ ይጥራው፤ ይህን ዘመነ መንሱት፤*
*ይህን ዘመነ - ፈተና?*
*ይበቅል ይሆን ከዚህ ጠፍ ላይ፤ ከዚህ መና ከዚህ ወና*
*ተስፋ ማድረግን እሚያውቅ ኅልው፤ ሣቅን እሚያቅ ስብእና*
*የሰላም ሪቅ የጤና፤ የፍቅር አንድነት ጋዘና…*
*ይበቅል ይሆን?*
*በትንሣዔ እንድናምን፤ ያሸት ይሆን አዝመራው?*
*ያፈሩ ይሆን ተክሎቹ? ያብቡ ይሆን ዕፅዋቱ?*
*ይተሙ ይሆን ንቦቹ? ይዘምሩ ይሆን ወፎቹ?…*
*በትንሣዔ እንድናምን፤*
*ይደራ ይሆን ከከበጽባህ፤ የእንቁጣጣሽ ችቦ*
*በእምነት በአለኝታ ጉንጉን ተውቦ፤ በቀስተ ደመና ተከቦ*
*ተሞሽሮ በፀደይ ወርቀ ዘቦ፤…*
*ይደራ ይሆን?*
*ይኖር ይሆን ወይ አርማ፤ ይኖር ይሆን ወይ ባንዲራ፤*
*ሰውን የመሰለ ቀለም ያለው፤ ሰውን የመሰለ አሻራ፤*
*እማይወድቅ፤ እማይታጠፍ ሰንደቅ፤ እማይከስም፤*
*እማይዳፈን ደመራ?…*
*ይኖር ይሆን?. . ."*
*እንዲኖር የነገውን ሰው፡- ወጣቱን እንመልከት።*

*አመሰግናለሁ።*

*ነሲቡ ስብሐት*

*የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ.ም.*

***ግጥሙ፦*** *ነፍሱን ይማርና ከደራሲ፣ ገጣሚ፣ የሥነ ጽህፍ ተመራማሪውና ሃያሲ ደበበ ሰይፉ* **የግጥም መድበል የብርሃን ፍቅር ቁጥር 1 "ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ" ከሚለው የምዕተ ዓመቱ ብርቅዬ ግጥም የተቀነጨበ ነው።**